የጥልቅ ተሃድሰውን ትኩረት የሚሻው

የልማት ዘርፍ

ዮናስ

በኢህአዴግ የሚመራው መንግስት ዘመናዊ ኢኮኖሚ በተለይም ዘመናዊ የገበያ ኢኮኖሚ ከፍተኛ የሸቀጦች ዝውውርን እና የሰዎችን ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ ሁኔታ የግድ አስፈላጊ እንደሆነ ማመን ብቻ ሳይሆን መርሁም እንደሆነ በተደጋጋሚ መናገሩ እንደተጠበቀ ሆኖ ድርጅታዊ ሰነዶቹም የፊት ለፊት አጀንዳቸው መሆኑ ይታወቃል። የአንድን ዘመናዊ የገበያ ኢኮኖሚ ቅልጥፍናና የውድድር ብቃት ከሚወስኑት ነገሮች አንዱ የትራንስፖርት አገልግሎቱ ቅልጥፍናና ውጤታማነት ነው። ሸቀጦችንና ሰዎችን በፍጥነት በገፍና በዝቅተኛ ወጪ ለማዘዋወር የሚችል የትራንስፖርt አገልግሎት ያለው ኢኮኖሚ በገበያ በብቃት መወዳደር የሚችል ሲሆን ይህንን ማድረግ ያልቻለ ኢኮኖሚ ደግሞ መወዳደር የማይችል እንደሆነ ሰኔ 2000 ላይ "አገራዊ ለውጦች፣ ቀጣይ ፈተናዎችና አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ መፍትሄዎች" በሚል ድርጅቱ ያዘጋጀው ሰነድ ያስቀምጣል። በሌላ በኩል በ1994 የወጣው የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ጉዳዮች ፖሊሲ የአገራችን ህዝቦች ብዝሃነት እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ጠንካራና የበለጸገ ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰብ ከመፍጠር አኳያ በመሰረተ ልማት ሁሉንም የአገራችንን አካባቢዎች ማስተሳሰር ወሳኝ ጉዳይ እንደሆነ አስምሮበታል።

በነዚህና በሌሎችም የድርጅቱና የመንግስት ሰነዶች የትራንስፖርት ዘርፍ የአገሪቱ የኢኮኖሚ የደም ስር ተደርጎ በመወሰዱ በአገራችን ባለፉት አመታት ፈጣን ልማት ማረጋገጥ መቻሉም የማይተባበል ነው ። በተለያዩ የአገራችን ብሄሮችና ብሄረሰቦች መካከል መተዋወቅ፣ መግባባትና መቀራረብን ፈጥሯል። ከአገር ውስጥ ግንኙነት አልፎ ከፍለአህጉራዊና አህጉራዊ ትስስሮችን መፍጠር የሚያስችለንን መልካም እድል አስገኝቷል። በአጭር አመታት ውስጥ ግዙፍ የትራንስፖርት አውታር መገንባት በመቻሉ በዚህ አመት የተከሰተውን ከባድ የድርቅ አደጋ ከወደብ ደራሽ እህልና አልሚ ምግብ በሚሊዮን ቶን በማጓጓዝ ለወገኖቻችን በወቅቱ ደርሶ መታደግ የተቻለውም ስለዚህና በመጣው ለውጥ ነው።

ድህነትን ለማጥፋት የሚያስችል ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ለማምጣት እንዲሁም ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለማስፋፋትና ህዝቡን ተደራሽ ለማድረግ እጅግ ወሳኝ ከሆነው ዘርፍ ደግሞ ከላይ የተመለከተው ውጤት እንደተጠበቀ ሆኖ በሰፋው ጉድለቱ የምናውቀው የመንገድ መሰረተ ልማት የዚህ ጽሁፍ አጀንዳና፤ ይልቁንም ጥልቅ ተሃድሰው ጥልቅ ትኩረት ማድረግ ከሚገባው ዘርፎች ቀዳሚው መሆኑን የሚመሰክር እና የሚመክር ነው ።

የመንገድ መሰረተ-ልማት ከተማውን ከምርት አካባቢዎች፣ የግብርና አካባቢዎችን ደግሞ ከገበያ ስፍራዎች ጋር በማገናኘት የአርሶ አደሩንም ሆነ የከተማ ነዋሪውን የጋራ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ወሳኝ ነው፡፡ በአገራችን ህዝቦች መካከል መቀራረብ፣ ያላቸውን በህገ-መንግስታችን የተቀመጠውን ራዕያቸውን ለማሳካት እንዲችሉ የመንገድ መሰረተ ልማት መስፋፋት የማይተካ ሚና አለው፡፡ ይህን የተገነዘበው በኢህአዴግ የሚመራው መንግስት ትክክለኛ የመንገድ ልማት ፖሊሲ በመቅረፅና ተገቢውን በጀት በመመደብ ላለፉት 25 አመታት ተግባራዊ ያደረጋቸው የመንገድ ልማት ፕሮግራሞች ለተገኘው ውጤት ዋነኛው ምክንያት መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

የደርግ መንግስትን መገርሰስ ተከትሎ ባሉት የመጀመሪያዎቹ 5 ዓመታት የአስቸኳይ ጊዜ የመንገዶች መልሶ ግንባታ ፕሮግራም በመንደፍ በጦርነት በተጎዱ አካባቢዎች የሚገኙ መንገዶች እንዲጠገኑ ከማድረጉ ጎን ለጎን አዳዲስ የአስፋልት፣ የጠጠር እና ገጠር መንገድ ግንባታዎች እንዲከናወኑ አድርጓል፡፡

ከዚህ በመቀጠልም ከ1989 ዓ.ም እስከየመጀመሪያውን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን ማብቂያ ድረስ አራት የመንገድ ልማት ፕሮግራሞች ተቀርፀው ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ በእነዚህ አራት ፕሮግራሞችም 118ሺ 550 ኪ.ሜ የሚረዝሙ አዳዲስ የአስፋልት፣ የጠጠር፣ የገጠርና የወረዳ መንገዶች ግንባታና የመንገዶች ከባድ ጥገና ስራዎች ተከናውኗል። ይህም መንግስት ሰፊውን ህዝብ በማሳተፍ በ100 አመታት የተገነባውን መንገድ 6 እጥፍ በ25 አመታት ውስጥ ለመገንባት እንደቻለ ተረጋግጧል ፡፡

በመንግስት ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸው በአስፋልት ደረጃ ከተገነቡት መንገዶች መካከልም ሀገራችንን ከጎረቤት ሀገራት ወደቦች ጋር የሚያገናኟት መንገዶች ይገኙበታል። በዚህም ሀገራችንን ከሰሜን ሶማሌላንድ፣ ከሱዳንና ከጅቡቲ ጋር የሚያገኛኙ መንገዶች ግንባታቸው የተጠናቀቀ ሲሆን ከኬንያ ጋር የሚያገኛኘን መንገድም በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል፡፡ በተጨማሪ አዲስ አበባን ከክልል ዋና ከተሞች እና ከሌሎች ትላልቅ ከተሞች ጋር የሚያገናኙ ነባር የጠጠር መንገዶች በአስፋልት ደረጃ ተገንብተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ናቸው፡፡

በእነዚህ 25 ዓመታት የተተገበሩት የመንገድ መሰረተ-ልማት ፕሮግራሞች ኢኮኖሚው በሁለት አሀዝ እንዲያድግ ያስቻሉ ከመሆናቸው ባሻገር ለዜጎች በርካታ ጠቀሜታዎችን አስገኝተዋል፡፡ የጤናንና የትምህርት አገልግሎቶችን የሚሰጡ ተቋማት በተለይም የጤና ኬላዎችንና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በቅርበት ገንብቶ ተደራሽ ለማድረግ የተቻለ ሲሆን የገጠሩ ነዋሪ ክረምት ከበጋ ከሚያስኬድ መንገድ ላይ ለመድረስ በአማካይ ይወስድበት የነበረውን ግዜ በአመካይ በ1 ሰዓት ለማሳጠር ማስቻሉንም የዘርፉ ባለሞያዎች መስከረዋል፡፡ እንዲሁም

አርሶ አደሩ የግብርና ግብአቶችን በአቅራቢያው እንዲያገኝ ያስቻሉት ሲሆን ትርፍ የግብርና ምርቶቹንም በቀላሉ ለገበያ በማቅረብ በተወዳዳሪ ዋጋ በመሸጥ ተጠቃሚ እንዲሆን አስችለውታል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በመሰረተ-ልማቱ የ25 አመታት የግንባታ ሂደት ውስጥ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች የስራ እድል ያገኙ ሲሆን በሺዎች የሚቆጠሩ አነስተኛ ኮንትራክተሮችን ለመፍጠርም በማስቻሉ በሃገራችን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ያለውን የጎላ ሚና አሳይቷል ተችሏል፡፡ ይህ ሚናው ግን ከዚህም የላቀ ሊሆን የሚገባውን ቦታና ይህ ባለመሆኑም ከላይ በተገለጸው ትርፍ መደመም ሳይገባን፤ ይልቁንም በዚህ ጥልቅ ተሃድሶ በጥልቀት መመልከት ያለብን ዘርፍ ይኸው የመንገድ መሰረተ ልማት ዘርፍ መሆኑን ከአስረጂዎች ጋር ማመላከት ደግሞ የዚህ ጽሁፍ አቢይ ጉዳይ ነው።

ቀደም ብለን እንደገለፅነው፣ በሃገራችን በስፋት ከሚታየው የልማት ተግባር አንዱ እና ዋነኛው የመንገድ መሠረተ ልማት ነው፡፡ የአንድ ሀገር ዋና ከተማ ካለው አጠቃላይ ስፋት ከ20 እስከ 25 በመቶ የሚሆነው በመንገድ መሠረተ ልማት መሸፈን አለበት ከሚለው ዓለም አቀፍ መለኪያ እና ስምምነት አንፃር ገጠሩ ቀርቶብን በክልል ከተሞቻችን ላይ  ብዙ መሥራት የሚጠበቅብን እንጂ የተሰሩት ብርቅ ሊሆኑብን ቀርቶ ተሰርተዋል ብሎ በድፍረት ለመናገር እንደማያበቁም ይህ ስሌት ይነግረናል ፡፡

ይህን ያህል መጠን የማድረስ ፍላጐት ከህዝቡ ዘንድ ሊመነጭ የሚችለው ህዝቡ በዘመናዊ የኑሮ ዕድገት ግስጋሴ ውስጥ በመሆኑ ሲሆን ዘመናዊ መንገድ ደግሞ የዕድገትና የስልጣኔ መለያ ስለሆነ ነው፡፡ ስለሆነም ዛሬ በየትኛውም የክልሎቻችን አቅጣጫ ይህን ህልም ዕውን ሊያደርግ የሚችል የመንገድ መሠረተ ልማት በስፋት እየተከናወነ ነው፡፡ ዘላቂ ምቾት በዋና ዋና ከተሞች ለመፍጠር የተጀመረውና በከፍተኛ ደረጃ እየተከናወነ በሚገኘው በዚሁ የልማት ሥራ ዋነኛ ተጠቃሚ ነዋሪው ህብረተሰብ ሲሆን የዚሁ ልማት ዋነኛ መነሻና መድረሻ ግብም ይኸው ህብረተሰብ ነው፡፡

ይሁን እንጂ ይህን መሰል ሰፊ የልማት ሥራ በሚከናወንበት ጊዜ በብዙ መልኩ የህዝብ አለመመቸትን ጨምሮ ከዚህ በላይ መስራት እንዳይቻል ያደረጉ፤  ምናልባትም ጥልቅ ተሃድሶ ሳያስፈልጋቸው በተራ ግምገማ ሊወገዱ ይገባቸው የነበሩ ችግሮች ዛሬም አብረውን በመዝለቅ ህዝብን አማረዋልና በጥልቅ ተሃድሶው ደግሞ ጥልቅ ትኩረት ሰጥተን ልንፈታቸው ይገባል።

አንደኛ ልማቱ ራሱ በለሙ ከተሞች መሀል ውስጥ በመከናወኑ ሲሆን ሌላውና መጠቀስ ያለበት ግን አሠራሩ ሁሉ ዘመናዊነትን ያልተላበሰና ለብልሹ አሰራር የተጋለጠ መሆኑ ነው። በመንገድ  መሰረተ ልማት ዝርጋታ ወቅት ህብረተሰቡ ላይ ከሚደርሱ እንግልቶች መካከል የግንባታው በወቅቱ አለመጠናቀቅና መጓተት፣ የሚቆፈሩ ቦታዎች በወቅቱ አለመሞላት፣ የቱቦ ቀበራ በፍጥነት አለመፈፀም፣ አቧራን ለመቀነስ ውሃ አለማርከፍከፍ፣ ለተሽከርካሪና ለእግረኛም ቢሆን ጊዜያዊ እና ተለዋጭ መተላለፊያ አለመስጠት፣ በልማቱ መርካት የሚገባውን ህብረተሰብ ምሬት ውስጥ የከተቱ ጉድለቶች መሆናቸው በተደጋጋሚ እና ይልቁንም በመንግስት ሚዲያ ላይ ሳይቀር የሰርክ ወሬ ሆኖ ሳለ ዝም ከተባለ በእርግጥም ጥልቁ ተሃድሶ ቀዳሚው አጀንዳ ሊያደርገው ይገባል ማለት ነው ፡፡

በሌላ በኩል ለግንባታዎች በጊዜ አለመጠናቀቅና መጓተት ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩም በተለይ ከውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን፣ ከኢትዮ ቴሌኮምና ከመብራት ኃይል ኮርፖሬሽን ጋር በተያያዙ የሚከሰቱትን ማየት ይቻላል፡፡ በመንገድ ግንባታ ሂደት መሬት የሚቀበሩ ወይም ከመሬት የሚወጡ የውሃና የፍሳሽ፣ የቴሌና የመብራት መሥመሮች ወቅቱን ጠብቀው ቢነሱ እና በቅንጅት ቢገነቡ የህዝቡን እንግልት መቀነስ ብቻ ሳይሆን በዚሁ ምክንያት የሚከሰተውን የሀገር ሀብት ብክነትም ማስቀረት ይቻላል፡፡

የወሰን ማስከበር ሥራዎች ምንም ተወዳዳሪ የሌላቸው የመንገድ ግንባታ ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ ሥራዎቹ በወቅቱ ከተጠናቀቁ ለግንባታዎች መፋጠን የሚኖራቸው ድርሻ መለኪያ የሌለውን ያህል በጊዜው አለመከናወናቸው ደግሞ ለመጓተቱም ሆነ ለህብረተሰቡ ምሬት ዋነኛ መነሻዎች መሆናቸውንም ጥልቁ ተሃድሶ ተገንዝቦ ጥልቀት ያለውና ዘላቂነት የሚኖረው እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ በየደረጃው የሚገኘው የአካባቢ መስተዳደርና የመንገድ ግንባታው ዋነኛ ተጠሪ የባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ የጋራ የቅንጅት ሥራ ለተግባሩ ውጤታማነት ወሳኝ መሆናቸውንም ጥልቁ ተሃድሶ ለይቶ የሚመጥኑትን ሊመድብ ይገባል፡፡

በዚሁ ሥራ ላይ የሚታየውን የምርት አቅርቦት ችግርንና በአንቀሳቃሾች ላይ የሚታየውን የሥነ - ምግባር ችግሮችን እንዲያቃልል ታሳቢ ተደርጎ በስራ ላይ የዋለው የኮብል ድንጋይ መንገድ ሥራም ጥልቁ ተሃድሶ በጥልቀት ሊያየው የሚገባው ዘርፍ ነው። በዚህ ላይ የሚታየውን የጥራት ችግር በማስወገድ በፍትሃዊ የልማት ተጠቃሚነት ህብረተሰቡን ማርካት የሚቻለውም በዚህ እና ጥልቁ ተሃድሶ በጥልቀት ፈትሾ በሚወስደው እርምጃ ብቻ ነው ።

ለመንገድ ግንባታ ዋነኛ ኢጋዥ የሆኑት የድንጋይ መፍጫ እና የአስፋልት ማምረቻ ፕላንቶች ቀደም ሲል ሠው የማይደርስባቸው ቢሆኑም አሁን በቤቶችና በመንደሮች ተከበዋል፡፡ በዚሁም ምክንያት በሚያመርቱበት ጊዜ በሚያወጡት አቧራ እና ጭስ ነዋሪው ተቸግሯል፡፡ ይህን ጉዳት መቀነስም የጥልቅ ተሃድሶው የቤት ስራ መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡

ከሁሉ በላይ ደግሞ የፌደራል መንግስቱን ጨምሮ ሁሉም ክልሎችና ሁለቱም የከተማ አስተዳደሮች ዘርፉ የሚመጥነውን እና በአገልግሎት ክልል ውስጥ ሆነው ከአገልግሎት መስጫ ክልል ውጪ የማይሆኑ ኮሙዩኒከተሮችን በቦታው ላይ ማስቀመጥ ወቅቱ የሚጠይቃቸውና ጥልቁ ተሃድሶም በጥልቀት ሊመለከተው የሚገባው ይሆናል።